የኮቪድ-19 ክትባት

# እውነታዎቹን ያግኙ።

## ክትባቶች ለሁሉም ሰው ነፃ ናቸው።



- ማንም ሰው መክፈል ካልቻለ፣ ክትባት ሊከለከል አይችልም።
- የኢሚግሬሽን ሁኔታዎ ምንም ይሁን ምን፣ መታወቂያ ወይም የህክምና መድን ሽፋን ቢኖርዎትም ባይኖሮዎትም ክትባቶች ለሁሉም ሰው በነፃ ይሰጣሉ።

## ክትባቱ በኮቪድ-19 እንዳይያዙ ይረዳዎታል።

- ከተከተቡም በኋላ በኮቪድ-19 ከተያዙ፣ ክትባቱ በጠና እንዳይታመሙ ይጠብቁዎታል።
- ከዚህ በፊት በኮቪድ-19 ተይዘው የነበረ ቢሆኑም እንኳ፣ አሁንም መከተብ አለብዎት።
- የማጠናከሪያ ክትባቶች መውሰድን ጨምሮ፣ የኮቪድ-19 ክትባቶችዎን ወቅታዊ ያድርጉ።



## የኮቪድ-19 ክትባቶች ደህንነታቸው የተረጋገጠ እና ውጤታማ ናቸው። ክትባቱ ኮቪድ-19 ንን ሊያስዝዎት አይችልም።

- በኮቪድ-19 ከመያዝ ክትባቱን መከተብ ይሻላል።
- በሚሊዮን የሚቆጠሩ ሰዎች ደህንነቱ በተጠበቀ መንገድ ተከትበዋል።
- በአሜሪካ ታሪክ ለደህንነቱ ይህን ያህል ሌላ ክትባት አልተመረመረም።
- ክትባቱ የተለያዩ ዘሮች፣ ጎሳዎች እና እድሜ ያላቸውን ሰዎች ጨምሮ በሺዎች በሚቆጠሩ ሰዎች ላይ ደህንነቱ ተረጋግጧል።
- የኮቪድ-19 ክትባት ዘረመልዎን (DNA) አይለውጠውም።



NRC-RIM
National Resource Center for Refugees, Immigrants, and Migrants

17 Aug 2022

ለበለጠ መረጃ፦ cdc.gov/coronavirus

# የጎንዮሽ ጉዳቶች የተለመዱ ናቸው።

**የጎንዮሽ ጉዳቶች ታዩ ማለት ኮቪድ-19 አለብዎት ማለት አይደለም።**

- የጎንዮሽ ጉዳቶች ማለት ክትባቱ ቫይረሱን እንዴት ኮቪድ-19 እንደሚዋጋ ሰውነትዎን እያስተማረ ነው ማለት ነዉ።
- የጎንዮሽ ጉዳቶች የሚከተሉትን ሊያካትቱ ይችላሉ፦
  - ክትባቱን በሚወጉበት ክንድዎ ላይ ህመም ወይም እብጠት።
  - ራስ ምታት ፣ ብርድ ብርድ ማለት ወይም ትኩሳት።
- ህመም ከተሰማዎት እስኪሻልዎት ድረስ ለጥቂት ቀናት ከሥራ እረፍት መውሰድ ይኖርብዎታል።
- ክትባት ከወሰዱ በኋላ አለርጂ እንዳልሆነብዎት ለማረጋገጥ ለ 15-30 ደቂቃዎች መቆየት ያስፈልግዎታል።

**የኮቪድ-19 ክትባቶች ጉርምስናን ወይም የወደፊት የመራባት ሁኔታ ላይ ተፅዕኖ አያሳድሩም።**

ወደፊት ልጆች መውለድ ለሚፈልጉ እና ለነፍሰ ጡር ወይም ጡት ለሚያጠቡ ሰዎች ክትባቶች ደህንነታቸው የተጠበቀ ነው።

## ክትባቶችዎን ወቅታዊ ያድርጉ።

- የኮቪድ-19 ክትባቶች ከከባድ ህመም፣ ሆስፒታል ከመተኛት እንዲሁም ከሞት ይከላከላሉ።
- ከፍተኛውን ጥብቃ እንዲያገኙ፣ የኮቪድ-19 ክትባቶችን ወቅታዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው።
- ክትባትን ወቅታዊ ማድረግ ማለት ሁለቱንም የባለ ሁለት- መርፌ ክትባት ዶዞችን መውሰድ እና ከዚያም እርስዎ ብቁ የሆኑባቸውን ማንኛውንም የማጠናከሪያ ክትባቶች መከተብ ማለት ነው።
- ክትባትዎን ወቅታዊ ካላደረጉ፣ በኮቪድ-19 የመያዝ፣ በጠና የመታመም ወይም የመሞት እንዲሁም ወደሌሎች የማዛመት ዕድልዎ ከፍተኛ ነው።

## ክትባቶች: የምከተሉትን አያካትቱም

- እንዲቆይ የሚያደርጉ ነገሮች
- እንቁላል
- የአሳማ ሥጋ ውጤቶች
- ጄልቲን
- ላቴክስ
- ማንኛውም በህይወት ያለ የኮቪድ-19 ቫይረስ

## ክትባቱን ከወሰዱም በኋላ ደህንነትዎን ጠብቀው ይቆዩ።

በአሁኑ ጊዜ፣ ባለሙያዎች ክትባቱ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚጠብቅዎት አያውቁም። ክትባቱን ከወሰዱ በኋላም ቢሆን፣ እነዚህን ማድረግ ይቀጥሉ፦

- ጭምብል መልበስ።
- አካላዊ ርቀትን መጠበቅ።
- እጅዎን ብዙ ጊዜ መታጠብ።
- ከፍተኛ ንክኪ ያላቸውን አካባቢዎች በተደጋጋሚ ማጽዳት።

NRC-RIM
National Resource Center for Refugees, Immigrants, and Migrants

ለበለጠ መረጃ፦ cdc.gov/coronavirus